የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ—ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 11
ADDIS ABABA—17th January, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፭/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ለሁለተኛው የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ............... ገጽ ፩ሺ፮፻፹፪

## CONTENTS

Proclamation No. 265/2002
African Development Fund Loan Agreement for Financing the Second Structural Adjustment Program Ratification Proclamation ........................ Page 1682

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፭/፲፱፻፺፬

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ዩ·ኤ· ፷ ሚሊዮን (ስድሳ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፭/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO. 265/2002*

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND*

*WHEREAS,* a Loan Agreement betwen the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of UA 60,000,000 (sixty million Units of Account) for financing the Second Structural Adjustment Program, was signed in Abidjan on the 16th day of November, 2001;

*WHEREAS,* basic economic international agreements have to be ratified prior to entry force;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at it's session held on the 17thday of January, 2002;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''African Development Fund Loan Agreement for Financing the Second Structural Adjustment Program Ratification Proclamation No. 265/2002.''

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪፻፻፩ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር 2100150006680 የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ·ኤ· ፷ ሚሊዮን (ስድሣ ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement Number 2100150006680 signed in Abidjan on the 16th day of November 2001, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of UA 60,000,000 (sixty million Units of Account) in the accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 17th day of January, 2002.

Done at Addis Ababa, this 17th day of January, 2002.

*GIRMA WOLDEGIORGIS*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE